
# ምዕራፍ አስር

## የፍልስፍና ሚና



### የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፤


- ❖ ስለ ፍልስፍና ምንነትና በዓለማችን እድገት ውስጥ ያለውን ሚና ደረጃውን በጠበቀ የኢ.ምቋ ታስረዳላችሁ፤
- ❖ ከፍልስፍና ጋር የተያያዙ የኢ.ምቋ ምልክቶችን በዕለት-ተእለት ተግባቦታችሁ ውስጥ ከነሥነምልክታዊ ውበታቸው ትጠቀማላችሁ፤
- ❖ ስለአንድ ታዋቂ ፈላስፋ መረጃ አሰባስባችሁ በክፍል ውስጥ በኢ.ምቋ ታቀርባላችሁ፤
- ❖ ስለኢትዮጵያ ቋንቋዎች ግንዛቤ ትጨብጣላችሁ።
- ❖ ገላጭ ምልክቶችን በተግባቦት ውስጥ ከቀድሞ በተሻለ ብቃት መጠቀም ትጀምራላችሁ።


## ቁልፍ ምልክቶች



ፍልስፍና


ሂደት


የሙያ መስክ



ህዋ


ፊልፍሎ



ሊደመደም


አያሌ



መንኮራኩር



ዝነኛ



ክህሎት




ጥበብ




አመክንዮ



መቅረጽ/ለፕሮግራም



መንፈሳዊ




## ክፍለ ትምህርት አንድ

### የማነቃቂያ ተግባር

#### እይታዊ ንባብ

የሚከተለውን ስዕል በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ አስረዱ።



**የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች**

1. ፍልስፍናን እንዴት ትተረጉሙታላችሁ?

2. ፍልስፍና ጠቀሜታ አለው ብላችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ?

## ምንባብ

መምህራችሁ **የፍልስፍና ሚና** የሚለውን ምንባብ ሲያነቡ ሐሳቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን የምልክት አጠቃቀማቸውን በጥንቃቀቄ ተመልከቱ።

### የፍልስፍና ሚና

ከሁሉም ነገር ጀርባ ፍልስፍና አለ ቢባል ማጋነን አይሆንም። ምክንያቱም ሁሉም ነገር የሚጀምረው ደረጃው ከተለያየ ፍልስፍና ነው። አንዳድ ጊዜ ያልገቡንን ነገሮች በተመለከተ ለምን ሆነ? እንዴት ሆነ? ወዘተ እያልን ራሳችንን ስንጠይቅና የጥያቄዎቻችን መልስ ሊሆኑ ይችላሉ ብለን የምንገምታቸውን መላምቶች የምንደረድርበት ሂደት ፍልስፍና ነው። በዚህም ምክንያትም ብዙውን ጊዜ እኛን የማይመለከት ቢመስለንም ፍልስፍና በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ትልቅ ሚና ያለው መስክ ነው።

ዛሬ የሰው ልጅ ለደረሰበት እውቀትና ቴክኖሎጂ ሁሉ ፍልስፍና ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ምክንያቱም የተገኘው እውቀትና ቴክኖሎጂ መሰረቱ ሰው ለምንና እንዴት ብሎ መጠየቁና ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ፍለጋ ያደረገው ጥረት ነው። ይህ ደግሞ ፍልስፍና ነው። የሰው ልጅ ያሰመዘገባቸውን ስኬቶችም ሆነ በሰው ልጆች መካከል የሚስተዋሉትን የሐሳብ ልዩነቶች ብንመረምር ጅምራቸው ፍልስፍና እንደሆነ መረዳት እንችላለን።

የሰው ልጅ በሕዋ ምርምር ያስመዘገባቸውን ስኬቶች እንደ ምሳሌ ብንወስድ ጅምሩ ፍልስፍና እንደሆነ እንረዳለን። ሰዎች ሕዋ ውስጥ ምን አለ? ብለው በመጠየቃቸውና ለዚህም መልስ ለማግኘት ባደረጉት ጥረት መንኮራኩር ሰርተው ወደ ጨረቃና ማርስ በመጓዝ ለተለያዩ ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ችለዋል። ስለዚህ በህዋ ምርምርና እውቀት ዘርፍ ዛሬ አለም ለደረሰችበት ደረጃ መሰረቱ ፍልስፍና ነበር ማለት ነው። ሌሎች ስኬቶችንም ብንመረምር በተመሳሳይ ሁኔታ ጅምራቸው ፍልስፍና ነው።

በተመሳሳይ መንገድም በሰዎች ወይም በሀገሮች መካከል የሀሳብ ልዩነቶችን የመፈጠሩ እና ይህንኑ ተከትሎ ለሚመጡ አለመግባባቶችና ግጭቶች መሠረታዊ ምክንያቱ የፍልስፍና መለያየት ነው። ሁሉም ሀገሮች ከሚከተሉት የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ሥርዓት ጀርባ ፍልስፍና አለ። ይህ የፍልስፍና ልዩነትም ዓለማችንን በሁለት ዋናዋና ጎራ ክፍሏታል። እነዚህ ጎራዎችም የምሥራቁና የምዕራቡ ዓለም በመባል ይጠቀሳሉ። ይህን ልዩነት የፈጠረው በዋናነት መልክአ-ምድራዊ አቀማመጣቸው ሳይሆን፣ በእነዚህ የዓለም ክፍሎች ያሉ ሀገራት የሚከተሉት ፍልስፍና ነው።የምዕራቡ ዓለም ፍልስፍና የጀርባ አጥንት አመክንዩ በመሆኑ የማያውቁትን ለማወቅ ይመራመራሉ። የሚያምኑትም ሊጨበጥ የሚችል አሳማኝ መረጃ ሲያገኙ ብቻ ነው። የምዕራቡ ፍልስፋና በእውቀትና በመረዳት ላይ የተመሰረተ ነው። ስለዚህ እውቀት ማለት በበቂ ምክንያት የተደገፈ እውነተኛ አምነት ነው ብሎ ያስተምራል። ማስረጃ ሊቀርብበት የማይችል ነገር ሁሉ ተአሚኒነት የለውም። ምዕራባውያኑ የሚከተሉት

የፖለቲካ፣ የማኅበራዊና የኢኮኖሚ ሥርዓትም ይህንኑ መሠረት አድርጎ የተቀረጸ ነው።

የምስራቁ ዓለም ፍልስፍና መሰረቱ ዕምነት ነው። ፍልስፍናው የተመሠረተው በእውቀት ላይ ሳይሆን ማስረጃ ሊቀርብበት በማይችል እምነት ላይ ነው። የምሥራቃውያኑ ፍልስፍና መሠረት ያለዕምነት የሚሆን ነገር ሁሉ ሐጢያት ነው የሚል ነው። ለምሥራቃውያኑ ፍልስፍና መሠረት የጥበብ ሁሉ መነሻና መድረሻ ፈጣሪ ነው የሚለው መንፈሳዊ አስተምህሮ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት የሚስተዋለው ፍልስፍና ወደ ምሥራቃውያኑ ፍልስፍና ያደላ በመሆኑ አንዳንድ ከእምነታችን ጋር የማይሄዱ ትምህርቶችን ወይም ልምዶችን ምዕራባዊ ነው ሲባል እንሰማለን።

በአጠቃላይ የፍልስፍና ሚና ከፍተኛ ነው። ፍልስፍና ሰዎች እውቀታቸውንና መረዳታቸውን እንዲያሳድጉና አዳዲስ ነገሮችን እንዲያገኙ ያግዛል። ፍልስፍና ሰዎች ምክንያታዊ እንዲሆኑ ይደግፋል። ይህን የማደርገው ለምንድነው ብሎ ራሱን በመጠየቅ የጀመረ ሰው ብዙውን ጊዜ ራሱን በስሜት ከመመራትና ከመሳሳት ሊያድን ይችላል። ወጣቶች የፍልስፍናን መርሆዎች በመከተል ለምን? እንዴት?በማለት መጠየቅ ከቻሉ ራሳቸውን በስሜት ከመመራትና በስህተት መንገድ ከመሄድ ከማዳን በተጨማሪ በአካባቢያቸውና በማኅበረሰባቸው ውስጥ ለሚያስተውሏቸው ችግሮች የመፍትሔ ሃሳቦች ማመንጨት ይቻላሉ። ይህ ደግሞ ሀገራችን ለምታልመው ብልጽግናና እድገት ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት እንዲያግዟችሁ ታቅደው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ።

1. በዚህ ምዕራፍ የመጫረሻ ክፍል ከፍ ሲል ከተነበበላችሁ ምንባብ ተወስደው ወደ ኢምቋ የተተረጎሙ ዐረፍተ ነገሮች ተቀምጠዋል። የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮቹን በሚገባ ካጠናችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንድ አንቀጽ ወስዳችሁ በኢምቋ አንብቡ።
2. መጽሀፎቻችሁን ሳትመለከቱ የምንባቡን መልእክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ አቅርቡ።

## መልመጃ ሁለት

*የሚከተሉት ጥያቄዎች የምንባቡን ሐሳብ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ለመመዘን የቀረቡ ናቸው። ጥያቄዎቹን በትክክል ለመመለስ መሞከራችሁ በዓይን የመስማት ብቃታችሁንም ለማዳበር ይረዳችኋል። ስለዚህ መምህራችሁ ጥያቄዎቹን በኢ.ምቋ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ ተመልከቱና፣ ተገቢ መልሶችን በኢ.ምቋ አቅርቡ።*

1. ከሁሉም ነገር ጀርባ ፍልስፍና አለ የሚባለው ለምንድነው?
2. ዛሬ የሰው ልጅ ለደረሰበት እውቀትና ቴክኖሎጂ ሁሉ ፍልስፍና ትልቅ ሚና አለው የሚባለው ለምንድነው?
3. የሰው ልጅ በሕዋ ምርምር ባስመዘገባቸው ስኬቶች የፍልስፍና ሚና ምን እንደሆነ በአጭሩ አስረዳ።
4. በምሥራቁና በምዕራቡ ዓለም ፍልስፍናዎች መካከል ያሉት ዋንኛ ልዩነቶች ምንድናቸው?
5. ኢትዮጵያ ውስጥ በስፋት የሚሰተዋለው ፍልስፍና የትኛው ነው? መልሱን በምሳሌ
6. ፍልስፍና ሰዎች ምክንያታዊ እንዲሆኑ የሚደግፈው በምን መንገድ ነው ?
7. “ፍልስፍና ሀገራችን ለምታልመው ብልጽግናና እድገት ጉልህ ሚና ይኖረዋል።” ይህን አባባል በምሳሌ አስደግፋችሁ አብራሩ።

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## መልመጃ አንድ

ስለአንድ ታዋቂ ፈላስፋ መረጃ አሰባስባችሁ በክፍል ውስጥ በኢ.ምቋ አቅርቡ። በምታዘጋጁት ታሪክ ውስጥ ከፈላስፋው ፍልስፍናዎች የተወሰኑ ምሳሌዎች አካቱ። በፈላስፋው ፍልስፍናዎች ላይ የግል አስተያየታችሁን አክሉበት።

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ምንባብ ሁለት

### በኢትዮጵያ ያሉ ቋንቋዎች

ኢትዮጵያ የብዙ ብሔረሰቦችና የብዙ ቋንቋዎች ሀገር ናት። በኢትዮጵያ ውስጥ ከ80 በላይ ብሔረሰቦች አሉ። የ1999 የሕዝብና የቤት ቆጠራ ሪፖርት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚነገሩት ቋንቋዎች ሰባ ያህል እንደሆኑ ቢያሳይም የቋንቋ አጥኚዎች የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋን ጨምሮ ቋንቋዎቹ ዘጠና ያህል እንደሚሆኑ ያምናሉ። እያንዳንዱ ክልል የራሱን የሥራ ቋንቋ የመምረጥ ሕገመንግስታዊ መብት አለው። ለብዙ አመታት የሥራ ቋንቋ ሆኖ በመቆየቱ በአሁኑ ወቅት በአብዛኛው የሀገራችን ክፍልና በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን የሚነገረው ቋንቋ አማርኛ ነው። በዚህ ምክንያትም በአሁኑ ወቅት የሀገራችን ዋንኛ የሥራ ቋንቋ ሆኖ እያገለገለ ነው። ይህም ኢትዮጵያን የራሳቸውን ቋንቋ በሥራ ቋንቋነት ከሚጠቀሙ ጥቂት የአፍሪካ ሀገራት መካከል አንዷ ያደርጋታል። ከአማርኛ ሌላ በኢትዮጵያ አፋን ኦሮሞ፣ ሱማልኛ፣ ትግርኛ፣ ሲዳሞኛ፣ ወላይትኛ፣ የጉራጌ ቋንቋዎች፣ አፋርኛ፣ ሐድያኛ፣ ጋሞኛ፣ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚነገሩት ቋንቋዎች አፍሮ-ኤስያዊ እና ናይሎ ሳህራዊ በሚባሉ ሁለት ዋና የቋንቋ ክፍሎች ሊካተቱ ይችላሉ። በአፍሮ-ኤስያዊ የቋንቋ ቤተሰብ ውስጥም ኩሻዊ፣ ኦሞአዊ እና ሴማዊ የሚባሉ ንዑስ ክፍሎች አሉ።

የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ብቻ ሳይሆኑ ቋንቋዎቹ ጭምር ረጅም የርስ በርስ ትስስር እንዳላቸው ማስረጃዎች ይጠቁማሉ። ሕገመንግስቱ ማናቸውም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በእኩልነት የመንግስት እውቅና ይኖራቸዋል ብሎ በመደንገጉ ሁሉም ቋንቋዎች በእኩልነት ይታያሉ። ብዙ የሀገራችን ቋንቋዎችም ለቋንቋው ባለቤቶች ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት መስጫነት እያገለገሉ ነው።

## መልመጃ አንድ

ከላይ የተቀመጠውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በቃል መልሱ

1. በኢትዮጵያ ውስጥ ስንት ቋንቋዎች አሉ ?
2. በኢትዮጵያ ውስት ካሉ ቋንቋዎች ዋና ዋና የሚባሉት ቋንቋዎች የትኞቹ ናቸው?
3. አማርኛ የሥራ ቋንቋ ሆኖ እንዲገለግል የተመረጠበት ምክንያት ምንድነው?

## መልመጃ ሁለት

የክልላችሁን የሥራ ቋንቋ እንዲሁም የየራሳችሁን የአፍ መፍቻ ቋንቋ በተመለከተ አጠር ያለ ሪፖርት አዘጋጅታችሁ በክፈል ውስጥ በኢምቋ አቅርቡ።

# ክፍለ ትምህርት አራት

## ገላጭ ምልክቶች ማስተዋወቂያ (ክፍል ሦስት)

1. ገላጭ የተቆለመመ ሸ (ገም:ሸቆ )

ይህ ገላጭ በአብዛኛው የሚያገለግለው መዳፍ ላይ ሊቀመጡ ለሚችሉ ትንሽና ቀላል ነገሮች ነው።

**ምሳሌ አንድ:**

**ኢምቋ:** *መለመን መለመን መጨረሻ  ሰጠ።*



*መለመን መለመን መጨረሻ ገም:ሸቆ ሰጠ።*

**አማርኛ:** ለምኜ ለምኜ በመጨረሻ ትንሽ ሰጠኝ።

2. ገለጭ ጥፍሮ (ገም:ጥ )



ይህ ገላጭ ምልክት በአብዛኛው የሚያገለግለው በቁጥር ለማስቀመጥ ለሚያስቸግሩ በአንድ አካባቢ ሰብሰብ ብለው ለሚገኙ ሰዎች ወይም ነገሮች ነው። ምሳሌ፤ ስብሰባ ላይ ያሉ ብዙ ሰዎች፣ የስታዲዮም ታዳሚዎች፣ ሜዳ ላይ የተበተነ ሰራዊት ወይም እንሰሶች ወዘተ።

**ምሳሌ**

**ኢምቋ:** *ደረሰ አካባቢ   ።*

*ደረሰ አካባቢ ገም:ጥ።*

**አማርኛ:** ስደረስ አካባቢው በሰው ተጥለቅልቆ ነበር።

**ኢምቋ፡** *መጣ ህዝብ*  

*መጣ ህዝብ ገም፡ፕ።*

**አማርኛ፡** *የመጣው ህዝብ በጣም ብዙ ነው።*

### 3. ገላጭ ምልክት ያጎነበሰ ሸ (ገም፡ያሸ  )

*ይህ ገላጭ ምልክት በአብዛኛው የሚያገለግለው መታጠፊያዎችንና አቅጣጫዎችን እንዲሁም ማዕዘኖችን ለማሳየት ነው።*

**ምሳሌ፤**

**ኢ.ምቋ፡** *መሄድ ትንሽ*  ።

*መሄድ ትንሽ ገም፡ያሸ።*

**አማርኛ፡** *ትንሽ ከሄድክ በኋላ ታጠፍ።*

### 4. ገላጭ ምልክት ግድም ሀ (ገም፡ግሀ  )

*ይህ ጥቅል ገለጭ ምልክት የሚያገለግለው ክብ የሆኑ ነገሮች አያያዝን ለማሳየት ነው፡ ለምሳሌ፤ ብርጭቆ፣ ጠርሙስ፣ ቱቦዎች ወይም ቱቦ መሰል ነገሮች፣ ግንድ፣ መነጽሮች (የሩቅ መመልከቻ መነጽርን ጨምሮ)፣ በመደራራብ ለወፈሩ ነገሮች (ብር፣ ወረቀት፣ ወዘተ) ነው።*

**ምሳሌ፡**

**ኢምቋ፡** *መኪና* ⇦   ⇨ *።*

*መኪና ገም፡ግሀ።*

**አማርኛ፡** *መኪናው እንደ ቱቦ ቀጭንና ረዥም ቅርጽ አለው።*

*በሁለት እጆች በሚሰራት ጊዜ የቆምን ነገር (ምሳሌ፡ ዛፍ ወይም ምሰሶ) ውፍረት ለማሳየት ያገለግላል።*

### 5. *ገላጭ ምልክት ጭብጦ (ገም፡ ጭ*  )

*ይህ ገላጭ ምልክት የሚያገለግለው በአብዛኛው ለጠንካራ፣ትልቅና ድቡልቡል ነገሮች፣ ለሚጨበጡ ነገሮች (ምሳሌ ጦር፣ ዱላ፣ አካፋ፣ ወዘተ)።*

**ምሳሌ፡**

**ኢምቋ፡** *ነጭ መውረድ* 

*ነጭ መውረድ ገም፡ጭ*

**አማርኛ፡** በረዶው በጣም ትላላቅ ነው።

## ክፍለ ትምህርት አራት

### የኢምቀ ናሙና ሰዋሰው

**ከዚህ በታች የተቀመጡት አማርኛ ዐረፍ ተነገሮች በሙሉ ‹‹የፍልስፍና ሚና›› ከሚለው ምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው። ናሙናዎቹን በጥንቃቄ ከተለማመዳችሁ በኋላ ወደ ምንባቡ በመመለስ በኢምቋ አንብቡ።**

1. **ኢምቋ፡** *ሁሉም ነገር ኋላ አለ ምን መፈላሰፍ ፍ-ል-ስ-ፍ-ና። ይሄ ትልቅ ማድረግ አይደለም ግን እውነት።*

   **አማርኛ፡** ከሁሉም ነገር ጀርባ ፍልስፍና አለ ቢባል ማጋነን አይሆንም።

2. **ኢምቋ፡** *አንድ አንድ ጊዜ የሆነ ነገር መረዳት አይደለም ከዛ እኛ ራስ መጠየቅ መጀመር- ለምን መሆን- እንዴት መሆን - አሃ- ከዛ መልስ መፈለግ መፈለግ ማሰብ ማሰብ ግምት ይሄ ይሄ መዘረዘር ሂደት ስም ምን መፈላሰፍ ፍ-ል-ስ-ፍ-ና።*

   **አማርኛ፡** አንዳድ ጊዜ ያልገቡንን ነገሮች በተመለከተ ለምን ሆነ? እንዴት ሆነ? ወዘተ እያልን ራሳችንን ስንጠይቅና የጥያቄዎቻችን መልስ ሊሆኑ ይችላሉ ብለን የምንገምታቸውን መላምቶች የምንደረድርበት ሂደት ፍልስፍና ነው።

3. **ኢምቋ፡** *መፈላሰፍ ፍ-ል-ስ-ፍ-ና መጀመር የት ጥያቄ ውስጥ። ጥያቄ ግን ራስ መሆን መቻል ወይም ሌላ ሰው መጠየቅ መቻል።*

   **አማርኛ፡** ፍልስፍና የሚጀምረው ከጥያቄዎች ውስጥ ነው። ጥያቄዎቹ ለራስ ወይም ለሌላ ሰው ሊሆኑ ይችላሉ።

4. **ኢምቁ:** *ሰው ማግኘት ስኬት ሁሉ መመርመር እንደገና ሰው መጋጠም ልዩ መሆን መመርመር ማግኘት ምን መጀመር የት- መፈላሰፍ ፍ-ል-ስ-ፍ-ና ማየት ቀላል።*

**አማርኛ:** የሰው ልጅ ያስመዘገባቸውን ስኬቶች ሆነ ያጋጠሙትን ልዩነቶች ብንመረምር ጅምራቸው ፍልስፍና እንደሆነ መረዳት እንችላለን።

5. **ኢምቁ:** *ምሳሌ ምን ሰው ሰማይ ሰፊ መመርመር ውጤት አገኘ ጀመረ እንዴት- መፈላሰፍ ፍ-ል-ስ-ፍ-ና ምሳሌ መሆን።*

**አማርኛ:**የሰው ልጅ በሕዋ ምርምር ያስመዘገባቸውን ስኬቶች እንደ ምሳሌ ብንወስድ ጅምሩ ፍልስፍና እንደሆነ እንረዳለን።

# የክለሳ ጥያቄዎች

**የኢ.ምቋ የተግባር ትምህርት በመሆኑ ጥያቄዎቹ የሚቀርቡት በተግባር ነው። ከኢ.ምቋ ትምህርት ውስጥ በጽሁፍ ቀርበው በማንበብና በመጻፍ መመለስ የሚቻሉ ጥያቄዎች ውስን ናቸው። ለእነዚህ ውስን ጥያቄዎች ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ የተወሰኑ የክለሳ ጥያቄዎች ከዚህ በታች ቀርበዋል።**

1. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የኢ.ምቋ ግሶችን ለየት ከሚያደርጓቸው ባህሪያት መካከል የሚመደብ አይደለም

   ሀ. እንደ አገባቡ ግስ ወይም ስም መሆን መቻል

   ለ. እንደ አገባቡ ግስ ወይም ቅጽል መሆን መቻል

   ሐ. የጊዜ አመልካች ቅጥያ መቀበል አለመቻል

   መ. ሁሉም መልስ ናቸው

   ሠ. መልሱ አልተሰጠም

2. *መቀመጥ መውደድ አይደለም።* በዚህ የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የ*መቀመጥ* ምልክት አገልግሎት ምንድነው?

   ሀ. ቅጽል

   ለ. ስም

   ሐ. ግስ

   መ. ተውላጠ ስም

   ሠ. መልሱ አልተሰጠም

3. *መቀመጥ የለም።* በዚህ የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የ*መቀመጥ* ምልክት አገልግሎት ምንድነው?

   ሀ. ቅጽል

   ለ. ስም

   ሐ. ግስ

   መ. ተውላጠ ስም

   ሠ. መልሱ አልተሰጠም

4. *መቀመጥ መውደድ አይደለም። ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች መካከል የዚህ የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገር ተቀራራቢ የአማርኛ ትርጉም የትኛው ነው?*

   *ሀ. መቀመጫ የለም*

   *ለ. መቀመጥ አልወድም*

   *ሐ. መቀመጥ ክልክል ነው*

   *መ. መቀመጫ የሚወድ የለም*

   ሠ. *መልሱ* አልተሰጠም

5. *ሞት መጥፎ።* በዚህ የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የ*ሞት* ምልክት አገልግሎት ምንድነው?

   ሀ. ቅጽል

   ለ. ስም

   ሐ. ግስ

   መ. ተውላጠ ስም

   ሠ. *መልሱ* አልተሰጠም

6. *ሞት ፍረሃት።* በዚህ የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የ*ሞት* ምልክት አገልግሎት ምንድነው?

   ሀ. ቅጽል

   ለ. ስም

   ሐ. ግስ

   መ. ተውላጠ ስም

   ሠ. *መልሱ* አልተሰጠም

7. *ሞት ፍረሃት ። ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች መካከል የዚህ* የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገር ተቀራራቢ የአማርኛ ትርጉም የትኛው ነው?

   ሀ. ሞት ጨካኝ ነው።

   ለ. ሞት ለምን ያስፈራል?

   ሐ. ሞት ያስፈራል?

መ. መሞት ያስፈራል::

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

8. *ቆንጆ ቆንጆ ሴት ሴት አየ።* በዚህ የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የ*ቆንጆ ቆንጆ* ምልክት አገልግሎት ምንድነው?

ሀ. ቅጽል

ለ. ስም

ሐ. ግስ

መ. ተውላጠ ስም

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

9. *ቆንጆ ቆንጆ ሴት ሴት አየ። ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች መካከል የዚህ* የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገር ተቀራራቢ የአማርኛ ትርጉም የትኛው ነው?

ሀ. አበበ ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች አየ።

ለ. ብዙ ቆንጆ ሴቶች አየሁ።

ሐ. ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች ማየት እፈልጋለሁ።

መ. ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች አይተሃል?

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

10. *ቆንጆ ቆንጆ ሴት ሴት አየ። ሴት ሴት ቆንጆ ቆንጆ መውደድ። በሁለቱ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ቆንጆ ቆንጆ ምልክት ልዩነት ምንድነው*

ሀ. በመጀመሪያው ዐረፍ ተነገር ውስጥ አገልግሎቱ ግስ ሲሆን፣ በሁለተኛው ዐረፍተ

ነገር ውስጥ ግን ቅጽል ነው።

ለ. በመጀመሪያው ዐረፍ ተነገር ውስጥ አገልግሎቱ ቅጽል ሲሆን፣ በሁለተኛው

ዐረፍተነገር ውስጥ ግን ግስ ነው።

ሐ. በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ውስጥ መጀመሪያ ሲመጣ በሁለተኛው ዐረፍተ

ነገር ውስጥ ግን የመታጣው በመጨረሻ ላይ ነው፡

መ. በመጀመሪያው ዐረፍ ተነገር ውስጥ አገልግሎቱ ስም ሲሆን፣ በሁለተኛው

ዐረፍተ ነገር ውስጥ ግን ግስ ነው።

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

11. *ሴት ሴት ቆንጆ ቆንጆ መውደድ። ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች መካከል የዚህ የኢ.ምቋ* ዐረፍተ ነገር ተቀራራቢ የአማርኛ ትርጉም የትኛው ነው?

ሀ. ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች እወዳለሁ።

ለ. ሴቶች መቆነጃጀት ይወዳሉ።

ሐ. ቆንጆ ቆንጆ ሴቶች ተወዳጅ ናቸው።

መ. ሴቶች ቆንጆ ቆንጆ ነገር ይወዳሉ።

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

12. በሚከተሉት የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረበት ምልክት አገልግሎት ግስ ነው።

*ሀ. መቆም ዝም ጥሩ አይደለም።*

*ለ.መቆም ነገር የለም።*

*ሐ. ሴት ሴት ቆንጆ ቆንጆ መውደድ።*

*መ. ሞት ፍረሃት*

*ሠ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው*

13. ከሚከተሉት አንዱ ‹‹እበላለሁ››ን ይወክላል፤

ሀ. የመብላት ምልክት + *በኋላ*

ለ. የመብላት ምልክት + *ወደፊት*

ሐ. የመብላት ምልክት + *መጨረስ*

መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

14. ከሚከተሉት አንዱ ያለፈ ክንውንን ይወክላል፤

ሀ. የመብላት ምልክት + በኋላ

ለ. የመብላት ምልክት + ወደፊት

ሐ. የመብላት ምልክት + መጨረስ

መ. ሀ እና ለ መልስ ናቸው

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

15. ከሚከተሉት አንዱ የኢ.ምቋ ግስ አይደለም፤

ሀ. ግልጽ ግስ

ለ. አላፊ ግስ

ሐ. አመልካች ግስ

መ. ገላጭ ግስ

16. ከሚከተሉት አንድ እንደ አገባቡ ግስ ወይም ስም ሊሆን ይችላል

ሀ. ማሽተት

ለ. ማየት

ሐ. መስማት

መ. መሽናት

ሠ. ሁሉም

17. የ‹‹ሀገር›› ምልክትን ወደ ቅጽል ለመቀየር፤

ሀ. የ‹‹መጨረስ›› ምልክት ይጨመራል

ለ. የ ዊ ማሳያ ይጨመራል

ሐ. የ‹‹ወደፊት›› ምልክት ይጨመራል

መ. የ‹‹እኛ›› ምልክት ይጨመራል

ሠ. መልሱ አልተሰጠም።

18. ከሚከተሉት አንዱ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን አይገልጽም፤

ሀ. የሥነቃል አንድ ክፍል ናቸው።

ለ. ደራሲ የላቸውም፡

ሐ. ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፉ የመጡ የአንድ ማኅበረሰብ ገጠመኞች ጥርቅም ናቸው።

መ. የአንድ ህዝብ የጋራ ሀብት ናቸው።

ሠ. ሁሉም ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ይገልጻሉ።

19. *ወዳጅ - ዓይን ሁለቱ ትንሽ ስህተት በቂ። የዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ትርጉም፤*

ሀ. *ወዳጅ ዓይን ተመሳሳይ*

ለ. *ወዳጅ ቅሬታ ስሜት ቀላል ስለዚህ ጥንቅቅ ጥንቅቅ አስፈላጊ*

ሐ. *ወዳጅ ዓይን ስሜት ቀላል ስለዚህ ጥንቅቅ ጥንቅቅ አስፈላጊ*

መ. *ወዳጅ ዓይን ሁለት አለ*

ሠ. *መልስ የለም*

20. *‹‹ጨለማ አለ ማብራት፤ መከራ አጋጠም ዘዴ መፈለግ›› የዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ትርጉም፤*

ሀ. *ችግር ማስወገድ እንዴት- ጥበብ ጥቅም ዘዴ መፈጠር አስፈላጊ*

ለ. *ጨለማ መብራት ሁለት ተመሳሳይ*

ሐ. *ጨለማ አለ መከራ መምጣት ግድ*

መ. *መከራ ምክንያት ምን- ጨለማ*

ሠ. *መልስ የለም*

21. *‹‹ክረምት አለፈ- አለቀ ቤት ሥራ ሥራ ያስፈልጋል  አይደለም›› የዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ትርጉም፤*

ሀ. *ቤት አስፈላጊ መቼ- ክረምት ብቻ*

ለ. *አንድ ነገር አለፈ በቃ ቁጭት ቅጭት ስህተት*

ሐ. *ክረምት አለፈ ቤት መፈለግ መፈለግ ያስፈልጋል አይደለም*

መ. *ክረምት መምጣት በፊት ቤት መፈለግ መፈለግ አስፈላጊ*

ሠ. *መልስ የለም*

22. *‹‹መሥረቅ ሰው ሱስ ማርካት ማድረግ ምን- አየት አየት ዳቦ እንኳን አገኘ መላስ መላስ ዝም›› የዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ትርጉም፤*

ሀ. *መስረቅ ሰው ዳቦ ላስ ላስ መወደድ*

ለ. አንድ ሰው ልማድ አለ መልቀቅ አይደለም ማሰር

ሐ. መስረቀ ሰው ሱስ መጥፎ

መ. መሰረቅ ሰው ዳቦ መወደድ

ሠ. መልስ የለም

23. ‹‹ልብ እሱ ነጭ ማቡካት ማቡካት›› የዚህ ምሳሌያዊ አነጋገር ትርጉም፤

ሀ. ሊጥ መልክ ምን ነጭ

ለ. ምኞት ህልም ብዙ

ሐ. እሱ ነጭ ማቡካት ማቡካት ውድድ

መ. እሱ ጥቁር ማቡካት መውደድ አይደለም

ሠ. መለስ የለም

24. ከሚከተሉት አንዱ የዝናብ ምልክት ቅጽል ምልክት ነው

ሀ. ዝናብ ዝናብ

ለ. ዝናባማ

ሐ. ዝናብ + ወደፊት

መ. ዝናብ + ገና

ሠ መልስ የለም

25. ‹‹ቂመኛ›› ቅጽል ምልክት ነው፣ ከሚከተሉት አንዱ የዚህ ምልክት ‹‹ስም›› ነው

ሀ. ቂሞች

ለ. ቂም

ሐ. ቂም ያዘ

መ. ቂም መጥፎ

ሠ. መልስ የለም

26. ቋሚ አቅጣጫና እንቅስቃሴ ያላቸው በሁሉም ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በተመሳሳይ መንግድ የሚሰሩ ግሶች ምን ተብለው ይጠራሉ?

ሀ. አመልካች ግሶች

ለ. ግልጽ ግሶች

ሐ. ዋና ምልክቶች

መ. ገላጭ ግሶች

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

27. ከሚከተሉት ምልክቶች መካከል የግልጽ ግሶች ምሳሌ የሆነው ምልክት የትኛው ነው?

ሀ. መብላት

ለ. መጠጣት

ሐ. መጠበቅ

መ. ማሰብ

ሠ. ሁሉም መልስ ናቸው

28. በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የግልጽ ግሶችን ትርጉም መረዳት የሚቻለው እንዴት ነው?

ሀ. ከአቅጣጫቸው

ለ. ከአገባባቸው

ሐ. ከፊት ገለጻና አካላዊ እንቅስቃሴዎች

መ. ሀ እና ሐ

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

29. ግራበማጋባት ላይ የተመሠረቱ ቃላዊ ግጥሚያዎች ናቸው

ሀ. ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ለ. እንቆቅልሾች

ሐ. ግልጽ ግሶች

መ. ገላጭ ግሶች

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

30. *ከላይ ነፍስ የለም- ሞት ከታች ነፍስ የለም- ሞት መሃል ምን- ነፍስ ማዳን መቻል አለ ምን።*

*ሀ. ዳቦ፣ አትክልት፣ ዳቦ*

*ለ. ቆርቆሮ፣ ቤት፣ ጊድጊዳ*

*ሐ. አክንባሎ፣ ምጣድ፣ እንጀራ*

*መ. መጽሀፍ፣ ስክሪቢቶ፣ እርሳስ*

*ሠ. መልሱ አልተሰጠም*

31. *እናት ሆድ መውጣት እንደ,ጋና እናት ራስ መርገጥ ምን*

*ሀ.* ጥጃ

ለ. አህያ ትንሽ

ሐ. የክብሪት እንጨት

መ. ዘነዘና

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

32. *የሙያ ምልክት + ባለቤት ምልክት = --------------------*

ሀ. ሙያ ባለቤት

ለ. ባለሙያ

ሐ. *ጎበዝ*

*መ. ሠነፍ*

*ሠ. ከ መ በስተቀር ሁሉም መልስ ናቸው*

33. እንደሚወክሉት ነገር የሚለዋወጡና ቋሚ የሚባል የእጅ ቅርጽም ሆነ አቅጣጫ የሌላቸው ግሶች ምን ተብለው ይጠራሉ?

ሀ. አመልካች ግሶች

ለ. ግልጽ ግሶች

ሐ. ዋና ምልክቶች

መ. ገላጭ ግሶች

ሠ. መልሲ አልተሰጠም

34. ቋሚ አቅጣጫና እንቅስቃሴ የሌላቸውና በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ እንዳላቸው አገባብ የሚለዋወጡ ምን ተብለው ይጠራሉ?

ሀ. አመልካች ግሶች

ለ. ግልጽ ግሶች

ሐ. ዋና ምልክቶች

መ. ገላጭ ግሶች

ሠ. መልሲ አልተሰጠም

35. ከሚከተሉት የግስ ምልክቶች መካከል ገላጭ ግስ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. መቆም

ለ. መውሰድ

ሐ. መምታት

መ. መጓዝ

ሠ. ሁሉም መልስ ናቸው

36. ከሚከተሉት የግስ ምልክቶች መካከል የአመልካች ግስ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. መበደር

ለ. መክፈል

ሐ. መቆም

መ. መውሰድ

ሠ. ሀ እና ለ

37.  ይህ ምልክት የሚሠራው በየትኛው አገባብ ውስጥ ነው?

ሀ. መኪና መቆም ክልክል።

ለ. ሰው መቆም ነውር።

ሐ. ሥራ መቆም ሕግ ቅጣት።

መ. በሁሉም ውስጥ

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

38.  ይህ ምልክት የሚሠራው በየትኛው አገባብ ውስጥ ነው?

ሀ. መኪና መቆም ክልክል።

ለ. ሰው መቆም ነውር።

ሐ. ሥራ መቆም ሕግ ቅጣት።

መ. በሁሉም ውስጥ

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

39. ‹‹ምግብ መዉሰድ›› በዚህ የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የመውሰድ ምልክት፤

ሀ. እጅ ከታች ተነስቶ እየታጠፈ ይመጣና አፍ አካባቢ ይቆማል

ለ. የ መውሰድ ምልክት

ሐ. የመብላት ምልክት

መ. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ የመውሰድ ምልክት

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

40.  ይህ ምልክት የሚሠራው በየትኛው አገባብ ውስጥ ነው?

ሀ. ላበድርህ

ለ. አበድርሃለሁ

ሐ. አበድረኝ

መ. አላበድርም

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

41.  ይህ ምልክት የሚሠራው በየትኛው አገባብ ውስጥ ነው?

ሀ. ላበድርህ

ለ. አበድርሃለሁ

ሐ. አበድረኝ

መ. ሀ እና ለ

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

42. የ‹‹ሕግ›› ምልክት + የ‹‹መስበር›› ምልክት = የ_______________ ምልክት

ሀ. ሕግሰባሪ

ለ. ሕገወጥ

ሐ. ሕግአስከባሪ

መ. ወንጀለኛ

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

43. የ‹‹ሁሉም›› ምልክት + የ‹‹ሚኒስትር›› ምልክት = የ______________ ምልክት

ሀ. ሚኒስትሮች

ለ ጠቅላይ ሚኒስትር

ሐ. መንግሰት

መ. የመንግስት ባለስልጣን

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

44. ከስሞችና ከግሶች ጋር በመምጣት ስሞቹን ወይም ግሶቹን የበለጠ ግልጽ የሚያድርጉና ትርጓሜን የሚያሳዩ ምልክቶች _____________ ይባላሉ።

ሀ. ገላጭ ምልክቶች

ለ. ግልጽ ግሶች

ሐ. ዋና ምልክቶች

መ. ገላጭ ግሶች

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

45. ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ስለ ገላጭ ምልክቶች እውነት የሆነው የትኛው ነው

ሀ. የአንድን ነገር መጠንና ቅርጽ ያሳያሉ፣

ለ.አንድን ነገር በመወከል ያሳያሉ፣

ሐ.የአንድን ነገር እንቅስቃሴ ሁኔታ ያሳያሉ

መ.አንድ ነገር ከሌሎች ነገር ጋር ያለውን ግንኙነት ያሳያሉ

ሠ. ሁሉም መልስ ናቸው

46. ገም፡3 ማለት ምን ማለት ነው

ሀ. 3 ገላጭ ምልክቶች

ለ. 3ኛው ምልክት

ሐ. ገላጭ ምልክት ሦስት ቁጥር

መ. ግምገማ 3

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

47. ገም፡ግሀ ምንን ይወክላል

ሀ. ገለጭ ምልክት ጥፍሮ

ለ.ገላጭ ምልክት ምልክት ያጎነበሰ ሸ

ሐ. ገላጭ ምልክት ምልክት ግድም ሀ

መ. ገላጭ ምልክት ምልክት ጭብጠ

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

48. *ጨለማ ትኩር አየ ምን* ⇦  ። *ማለት*

*ሀ. ጨለማ ትኩር አየ ምን- አንድ ሰው*

*ለ. ጨለማ ትኩር አየ ምን- አንድ ሰው መሄድ*

*ሐ. ጨለማ ትኩር አየ ምን- አንድ ሰው ወደ እኔ ሲመጣ*

*መ. ጨለማ ትኩር አየ ምን- አንድ ሰው ቆሞ*

*ሠ. መልሱ አልተሰጠም*

49. *ጨለማ ትኩር አየ ምን-* ⇦  ።

*ሀ. ጨለማ ትኩር አየ ምን- አራት ሰው*

*ለ. ጨለማ ትኩር አየ ምን- አራት ሰው መሄድ*

*ሐ. ጨለማ ትኩር አየ ምን- አራት ሰዎች በሰልፍ ወደ እኔ ሲመጡ*

*መ. ጨለማ ትኩር አየ ምን- አራት ሰዎች ጎን ለጎን እየተራመዱ ወደ እኔ ሲመጡ*

*ሠ. መልሱ አልተሰጠም*

50.የሚከተለው የኢምቋ ዐረፍተ ነገር ትርጉም ምንድነው ⇦   ⇨።

ሀ. አስር ሰዎች ወደ እኔ ሲመጡ

ለ. ብዙ ሰዎች ተሰልፈው ቆመዋል

ሐ. ብዙ ሰዎች ተሰልፈው እየሄዱ ነው

መ. አምስት ሰዎች ወደ ግራ አምስት ሰዎች ወደ ቀኝ ሲሄዱ

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

51. የሚከተለው የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገር ትርጉም ምንድነው?

⇦ ⇦ ፕ7:5:

ሀ. ሰዎች ወደ እኔ ሲመጡ

ለ. ሰዎች ተሰልፈው ቆመዋል

ሐ. ብዙ ሰዎች በሰልፍ እየሄዱ ነው

መ. አምስት ሰዎች ወደ ግራ አምስት ሰዎች ወደ ቀኝ ሲሄዱ

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

52. ‹‹  ⇨ ግንብ መጋጨት›› ማለት __________ ማለት ነው።


ሀ. ገም:3 ግንብ መጋጨት

ለ. መኪናው በኋላ ማርሽ ሲሄድ ከግንብ ጋር ተጋጨ

ሐ. መኪናው በፍጠነት እየተሽከረከረ ነው ከግንብ ጋር ተጋጨ

መ. ሀ እና ለ

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

53. ቢሮ መጽሐፍ  ። ማለት፤

ሀ. ቢሮው ውስጥ ሦስት ሰዎች ቆመዋል

ለ. ቢሮው ውስጥ መጽሀፎች አሉ

ሐ. ቢሮ መጸሀፍ ገም:ሸ

መ. ቢሮ ውስጥ መጽሐፎች ተገጥግጠዋል

ሠ. ሐ እና መ

54. በኢትዮጵያ ውስጥ ስንት ቋንቋዎች አሉ?

ሀ. 80 ለ. 90 አካባቢ ሐ. 15 መ. 100 ሠ. መልሱ የለም

55. አማርኛ የፌድራል መንግስት የሥራ ቋንቋ ሆኖ እንዲገለግል የተመረጠበት ምክንያት ምንድነው?

ሀ. ከሌሎች ቋንቋዎች የተሻለ ስለሆነ

ለ. በአብዛኞቹ ክልሎች ውስጥ ስለሚነገር

ሐ. ለብዙ ዓመታት የመንግስት የሥራ ቋንቋ ሆኖ በመቆየቱ

መ. ለ እና ሐ

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

56. በሕገመንግስቱ መሠረት፤

ሀ. ብዙ ተናጋሪ ያላቸው ቋንቋዎች ብቻ እውቅና ያገኛሉ

ለ. ሁሉም ቋንቋዎች በእኩልነት ይታያሉ

ሐ. በቋንቋዎች መካከል መበላለጥ አለ

መ. ከአማርናኛ የተሻለ ቋንቋ የለም

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

57. መለመን መለመን መጨረሻ --------- ሰጠ። በባዶው ቦታ መግባት የሚገባው ገም፤


ሀ. 

ለ. 

ሐ. 

መ. 

ሠ. መልሱ አልተሰጠም

58.  ። ማለት __________ ማለት ነው።

ሀ. ደረሰ አካባቢ ገም፡ጥ።

ለ. ስደረስ አካባቢው በሰው ተጥለቅልቆ ነበር።

ሐ. መቧጥጥ እወዳለሁ

መ. ሀ እና ለ

ሠ. መልሱ አልተሰጠም